Montgomery Planning

# የMontgomery የእቅድ ማውጣት ማስተር ፕላን ሂደት

## ለካውንቲው የወደፊት እጣ ፈንታ የእኛን የጋራ ራዕይ ለማሳደግ ይሳተፉ

### ማስተር ፕላን ምንድን ነው?

ማስተር ፕላን ያንን ራዕይ ለማስፈጸም እና የህይወት ጥራትን ለማሻሻል እንዲያግዝ ለመሬት አጠቃቀሞች፣ ለዞን አከላለል፣ ለመጓጓዣ፣ ለት/ቤቶች፣ ለፓርኮች፣ ለቤተ -መጻህፍት፣ ለእሳት አደጋ እና ለፖሊሲ ጣቢያዎች እና ለሌሎች እንቅስቃሴዎች ለወደፊት እጣ ፈንታ ራዕይን ያስቀምጣል።

በተጨማሪም ማስተር ፕላኖች የመኖሪያ ቤት፣ የታሪክ ማቆየትን፣ የእግረኛ እና የዱካ ስርዓቶች እንዲሁም የአካባቢያዊ ጉዳዮችን ይሸፍናሉ።

እነዚህ እቅዶች በህጋዊነት ጠቅላላ እቅዱን ያሻሽላል (Thrive Montgomery 2050 ተብሎም ይጠራል) እንዲሁም ካውንቲው እድገትን እንዴት እንደሚያጸድቅ፣ ቅድሚያ እንደሚሰጥ እና እንደሚቆጣጠር ይወስናል።

### ማቀዱ ለምን አስፈለገ?

Montgomery County ማደጉን ይቀጥላል እና የነዋሪዎች እና የጎብኚዎች ፍላጎቶች በሚመጡት አስርት አመታት ውስጥ መስተካከሉን ይቀጥላል—ስለሆነም ካውንቲው ቀስ በቀስ እየተለወጠ ከሚመጣው ማህበረሰብ ጋር ያለውን እርምጃ መጠበቁ አስፈላጊ ነገር ነው። ማስተር ፕላኖች ለሚቀጥሉት ከ15–20 አመታት የማህበረሰቡን ተፈላጊ ራዕይ ለመፍጠር ለህዝባዊ እና ለግል ዘርፎች መድረኩን ያመቻቻሉ።

እቅዱ ከጸደቀ፣ የካውንቲው ኤጀንሲዎች ለእድገት፣ ለፖሊሲ ዝግጅት፣ ለዞን አከላለል ለውጦች ያሉትን ኃሳቦች ያረጋግጣሉ እንዲሁም ለተቀመጠው ራዕይ በበለጠ ይገዛሉ። የMontgomery County መንግስት ከማህበረሰብ አባላት እና አልሚዎች ጋር በኤጀንሲዎቹ እና በአጋሮቹ በኩል ሰፊ የሆነ የዕቅድ አተገባበርን ያስተባብራል።

### መሳተፍ ለምን አስፈለገ?

ማስተር ፕላን ማውጣት ከማህበረሰብ ጋር ባለው ውይይት እና ትብብር ጋር በጠቅላላው የተመሰረተ ነው።

ግባችን የማህበረሰቡን ራዕይ የሚያንጸባርቁ የመጪ እድገቶችን የሚቀርጹ አሳቢ፣ ፈጣሪ እና ፍትሃዊ እቅዶችን መፍጠር ነው። ያንን የምናደርገው የነዋሪዎችን፣ የቢዝነሶችን እና የሌሎች መንደር ባለድርሻ አካላትን ፍላጎቶች፣ መጠይቆች እና እውነታዎች በማዳመጥ ነው።

ከዚያም፣ የማህበረሰብ ተስፋዎችን፣ ተግባራዊ እውነታዎችን በጋራ ለማምጣት እና ምርጥ ተሞክሮዎችን ለማቀድ፣ በካውንቲው ደንቦች፣ ቅድመ-ሁኔታዎች እና የፍትሃዊነት መነጽሮች ማዕቀፍ ስር ምርምር፣ ትንተና እና ልምድን እንተገብራለን።

**ጥሩ እቅድ ሁሉንም ተጫዋቾች በአንድ ገጽ ላይ ያቆያል ከዚያም ለሁሉም የተሻለ መጪ ጊዜን አልሞ እውን ለማድረግ ያግዛል።**

# የማስተር ፕላን ሂደት በወፍ-በረር እይታ

## የስራ ፕሮግራም

ስምምነት የተደረገባቸው ማስተር ፕላኖች ከካውንቲው ካውንስል ጋር በእያንዳንዱ የፀደይ ወቅት የበጀት ስምምነቶችን ተከትሎ ወደ Montgomery እቅድ ማውጣት ስራ ፕሮግራም ይታከላሉ።

## የስራው ቅድመ-ወሰን

እያንዳንዱ የማስተር ፕላን ማውጣት ጥረት ለበርካታ ወራት የተደረገ ዝርዝር የውሂብ ስብስብ፣ ቴክኒካዊ ትንታኔ እና የፕላን ወሰን ውሳኔን በመያዝ ይጀምራል። እነዚህ እንቅስቃሴዎች አሁናዊ ሁኔታዎችን ይገመግማሉ እና በጊዜ ቆይታ ይለወጣሉ፣ ይህም በአካባቢው ላይ ቁልፍ የሆኑ ጉዳዮችን የቀስ በቀስ ለውጥ ለመገንዘብ ለእቅድ አውጪዎች ይፈቅዳል።

## የሥራ ወሰን

የእቅድ ማውጣት ቡድኖች በእቅድ አውጪ ቦርዱ ለግምገማ እና ፈቃድ ወሰን ያቀርባል። የስራው ወሰን ከመጨረሻው የማስተር ፕላን ጀምሮ ያሉትን ለውጦች በመመርመር፣ ነባር ሁኔታዎችን ይዘረዝራል እና አዲስ የእቅድ ዝመና እና መሻሻል ለምን እንደሚያስፈልግ ያስረዳል። በተጨማሪም ወሰኑ በአዲሱ እቅድ ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ጉዳዮች ለዳሰሳ ያስቀምጣል።

## የራእይ ዝግጅት እና ትንተና

እቅድ አውጪዎች ከማህበረሰቡ ጋር ችግሮችን መለየት በመቀጠል መፍትሄዎችን መለየት ይጀምራሉ። የማህበረሰብ ውይይቶች ለእቅዱ ራዕይ እንዲጎለብት በመርዳት፣ የወደፊት የማህበረሰብ ሁኔታዎች፣ መሰረተ ልማት፣ የተገነባ አካባቢ፣ መገልገያዎች እና ሌሎችም እንዴት እንደሚሻሻሉ ይወያያል። በተጨማሪም እቅድ አውጪዎች ምርጥ ተሞክሮዎችን በመገምገም ለማህበረሰብ የሚያስኬዱ መንገዶችን የቤት ውስጥ እና ውጫዊ ልምድን ይተገብራሉ።

## የዕቅድ አውጪ ቦርድ ረቂቅ

እቅድ አውጪዎች ወደ እቅዱ ተጨማሪ የማህበረሰብ አስተያየቶችን በማካተት ለእቅድ አውጪ ቦርዱ የተከለሰ ረቂቅ ያቀርባሉ። ቦርዱ አዲሱን ረቂቅ ያጸድቃል እና ወደ ካውንቲ ካውንስሉ እና የካውንቲ ስራ አስፈጻሚው ለግምገማ ያስተላልፋል።

## የህዝባዊ ችሎት ረቂቅ እቅድ

እቅድ አውጪዎች ከእቅድ አውጪ ቦርዱ አስተያየቶችን ይወስዳሉ ከዚያም ኦፊሴላዊ ህዝባዊ አስተያየቶች ይገባል እና በህዝባዊ ችሎቱ ላይ የተከለሰ ረቂቅ ይቀርባል፣ በዚህም ጊዜ ማንኛውም ሰው ምስክርነት ሊሰጥበት ይችላል። በመሬት አጠቃቀም ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ስልጣን ያለው የእቅድ አውጪ ቦርዱ ምስክርነትን ለመገምገም የስራ ክፍለ ጊዜያትን እንዲሁ ሊይዝ እና የእቅድ አውጪ ቦርዱ የረቂቅ እቅድን ከማሳተም በፊት ማናቸውም ክለሳዎችን ማድረግ ይቻል እንደሆነ ለመወሰን ይችላል።

## የመስሪያ ረቂቅ እቅድ

እቅድ አውጪዎች የረቂቅ እቅዱን ያረቅቃሉ ይህም መጀመሪያ በማህበረሰብ ይገመገማል፣ ከዚያም ለእቅድ አውጪ ቦርዱ ይቀርባል።

## ቅድመ ምክረ ሃሳብ

እቅድ አውጪዎች አማራጭ እርምጃዎችን እና ምክረ ኃሳቦችን ለማስተር ፕላኑ ለማሳደግ ከማህበረሰቡ ጋር ይማከራል፣ ከዚያም እነዚህን ለእቅድ አውጪ ቦርዱ ያቀርባል።

## የካውንቲ ስራ አስፈጻሚ እና የካውንቲ ካውንስል ግምገማ እና ህዝባዊ ችሎት

የካውንቲ ስራ አስፈጻሚ በካውንቲ ካውንስሉ ላይ ያለውን እቅድ በተመለከተ ከማናቸውም አስተያየቶች እና ምክረ ኃሳቦች ጋር ፊዚካል የተጸዕኖ ትንተናን ያረቅቃል እንዲሁም ይልካል።

የካውንቲ ካውንስሉ እንደ አስፈላጊነቱ በእቅዱ ላይ ህዝባዊ ችሎትን ከዚያም የኮሚቴ ስራ ክፍለ ጊዜያትን ያደርጋል። ከዚያም ሙሉ የካውንቲ ካውንስሉ እቅዱ ላይ ይወያያል እና የስራ ክፍለ ጊዜያትን በማድረግ በሂደታቸው ውስጥ በተከሰቱ ማናቸውም ለውጦች ጋር የስራ ክፍለ ጊዜያትን ያደርጋል እና እቅዱን ያጸድቃል።

## ማጽደቅ እና ማሳደግ

Montgomery እቅድ ማውጣት እቅዱን በማረጋገጥ ለMaryland-National Capital Park and Planning Commission የመጨረሻ ማጽደቅ ለማድረግ ያስገባል። ከዚያም እቅዱ ለአጠቃላይ እቅዱ እና ለታተመው እንደ ማሻሻያ ሆኖ ይታከላል።

## የማስተር ፕላን አፈጻጸም

የMontgomery እቅድ ማውጣት ፍሬያማ እንዲሆኑ እቅዶችን ለማውጣት ሃላፊነቱን የሚወስዱ የካውንቲ ኤጀንሲዎችን የማማከር እና የምርምር ድጋፍን ቢሰጥም፣ እኛ ግን እቅዱን አንተገብርም። አንዴ እቅዱ ከረቀቀ፣ የMontgomery County መንግስት ከMontgomery County ኤጀንሲዎች እና አጋሮች ጋር በመሆን ከማህበረሰብ አባላት እና አልሚዎች ጋር እንደ ተገቢነቱ በመሄድ የእቅድ አፈጻጸምን ለማስተባበር ኃላፊነቱን ወስዷል።

*ማስታወሻ እዚህ ጋር የተዘረዘረው ለማስተር ፕላን ማውጣት ሂደቱ ሞዴል ሲሆን ይህም በአብዛኞቹ ኬዞች ውስጥ ይገዛል። ይሁን እንጂ፣ እያንዳንዱ ማህበረሰብ የተለየ ነው እና ከጊዜ ወደጊዜ እርምጃዎች ሊታከሉ፣ ሊሰረዙ ወይም ሊሻሻሉ ይችላሉ። እንደ እቅድ ማውጣት ቦርድ ችሎቶች፣ የካውንቲ ስራ አስፈታሚ ግምገማ ጊዜያት እና የካውንቲ ካውንስል ህዝባዊ ችሎቶች ያሉ በህግ አስገዳጅነት የተቀመጡ የእቅድ ማውጣት ሂደት ክፍሎች ለውጥ አይደረግባቸውም።*

**እንደተገናኙ ይቆዩ**

**በ**MontgomeryPlanning.org **ይጎብኙን** | **በ** Facebook.com/MontgomeryPlanning **ላይ ይውደዱን፣**
**በ**X @MontgomeryPlanning **ላይ ይከተሉን** | **ለ** ፓርኮች + እቅዶች ኤሌክትሮኒክ ደብዳቤ እና በMontgomeryPlanning.org/Connect ላይ ላሉት ለሌሎች ኤሌክትሮኒክ ደብዳቤዎች የደንበኝነት ምዝገባ ያድርጉ